# ደንብ

ሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች፦ AFA-RA, BLB, BLC, ECH-RA, IJA-RA, JFA, JFA-RA, JOA-RA, KLA-RA
ሃላፊነት ያለበት ቢሮ: ሃላፊነትን መጋራት
ተዛማጅ ምንጮች፦ የተማሪ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ 20 U.S.C፣ ሰክሽን 1232(h)፤ የፌደራል ደንቦች ኮድ፣ 34CFR 98.1 et seq፤ ምንም ልጅ ወደ ኋላ እንዳይቀር የሚደነግግ ህግ፣ ሰክሽን 1061

## በሚስጥራዊነት የሚጠበቅ የተማሪ መረጃን ስለመጠቀም የፌዴራል መስፈርቶች

I. ዓላማ

የዳሰሳ ጥናቶችን ማድረግ እና ፈተና መስጠትን በተመለከተ የግል መረጃን ለገበያ ማስተዋወቂያነት መጠቀም፣ እና አንዳንድ ቁሶችን መፈተሽ በሚመለከት የፌደራል ህግን ማክበር እና የተማሪ መብቶችን ጥበቃ ስለማድረግ።

II. ትርጉም

የሚከተሉት የፌደራል ህግ መመሪያዎች እና ትርጓሜዎች ለዚህ ደንብ JFF-RA የሚያገለግሉ ናቸው፥ በሚስጥራዊነት የሚጠበቅ የተማሪ መረጃን ስለመጠቀም የፌደራል መስፈርቶች ብቻ።

A. የተጠበቀ/ሚስጥራዊ መረጃዎች ማለት በሚከተሉት መደቦች ውስጥ የተካተቱ ስለ ተማሪዎች ህይወት የሚመለከቱ ዝርዝሮች ናቸው፦

1. ፖለቲካዊ ግንኙነቶች።

2. የተማሪ ወይም የተማሪ ቤተሰብ የአዕምሮ ወይም የስነ-ልቦና ችግሮች።

3. ፆታዊ/የፍትወተ ስጋ ፀባይ ወይም አመለካከቶች

4. ህገወጥ፣ ፀረ-ማኅበረሰብ፣ ራስን ወንጀለኛ የሚያደርግ፣ ወይም አዋራጅ ባህሪ።

5. የተማሪ ቤተሰብ አባላት ወሳኝ የባህርይ ግምገማዎች።

6. ጠበቆች፣ ዶክተሮች እና አገልጋዮችን የመሣሰሉ በህግ እውቅና የተሰጣቸው የተከበሩ/ልዩ ወይም ተመሳሳይ ግንኙነቶች።

7. የተማሪው/ዋ ወይም የተማሪው/ዋ ወላጆች ሐይማኖታዊ ተግባራት፣ ቁርኝት ወይም እምነቶች።

8. ለፕሮግራም ብቁነትን ለመወሰን ህግ ከሚጠይቀው ሌላ ገቢ።

B. ግላዊ የሰውነትን ገመና የሚጥስ አካላዊ ምርመራ ማለት፦ ማንኛውም የህክምና ምርመራ ሆኖ ሚስጥራዊ የሰውነት ክፍሎችን ማጋለጥን የሚያካትት፣ ወይም በምርመራ ወቅት የሚደረግ ድርጊት ሆኖ ሰውነትን እርቃን መክፈት፣ ውስጥ መከተት ወይም መውጋትን የሚያካትት ነው፣ ነገር ግን የማዳመጥ፣ የእይታ ወይም የስኮሊዎሲስ (scoliosis) መለያ ምርመራን አያካትትም።

C. ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ማለት፡- አስራ ስምንት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ እድሜ የሆኑ ተማሪዎች፣ ወይም ከወላጅ ተለይተው የሚኖሩ አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸው ታዳጊዎች ናቸው።

D. የትምህርት መሳሪያዎች ማለት፡- ለተማሪ የሚሰጡ የስርዓተ ትምህርት መሳሪያዎች ናቸው። ለወላጅ ቁጥጥር አላማ መሟላት ያለበት ነገር፡- የትምህርት ፈተናዎችን፣ የሙከራ ቴስት/ፈተና ወይም ምዘናዎችን አያካትትም።

E. የግል መረጃ ማለት፡- በግል ተነጥሎ የሚታወቅ መረጃ ነው፣ የሚያካትተውም፡-

1. የተማሪ ወይም የወላጅ የግል እና የቤተሰብ ስሞች፤

2. የተማሪ የቤት ወይም ሌላ አካላዊ አድራሻ (የመንገድ ስም እና ከተማ ወይም አካባቢን ጨምሮ)፤

3. የስልክ ቁጥር፤ እና፣

4. የሶሻል ሰኩሪቲ ቁጥር።

F. የዳሰሳ ጥናት ማለት፡-ጥበቃ የተደረገለት መረጃ መደቦችን በሚመለከት ስለ ተማሪ አመለካከቶች ወይም የግል አስተያየቶች የሚደረግ መጠይቅ ወይም ሌላ አይነት ጥያቄ ነው።

**III.** ሂደት/ቅደም-ተከተል

ወላጆች እና ብቁ የሆኑ ተማሪዎች የሚከተሉት መብቶች አሏቸው፡-

A. የተማሪ መብቶች ጥበቃ ማሻሻያ (PPRA) ስር ስለመብታቸው ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል።

B. ጥበቃ የተደረገለትን መረጃ በሚመለከት በፌደራል ፈንድ/የገንዘብ ድጋፍ በሚደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች ላይ ለመሳተፍ የሚደረግ ስምምነት። የዩኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት ለዳሰሳ ጥናት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የገንዘብ ድጋፍ ካደረገ፣ ተማሪው/ዋ በዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ ከመሳተፉ/ፏ በፊት የተማሪ ወላጆች ወይም ብቁ የሆነ ተማሪ በጽሁፍ መስማማት አለባቸው።

C. የተወሰኑ የዳሰሳ ጥናቶች እና የአካል ፈተናዎች ላይ ላለመሣተፍ መምረጥ ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለወላጆች እና ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ከሚከተሉት ተግባራት መካከል የትኛውንም በሚመለከት እና በተግባሮቹ ላይ ላለመሳተፍ የመምረጥ መብታቸውን በሚመለከት ማሳወቂያ ይሰጣል፡-

1. ጥበቃ የተደረገለት መረጃ ላይ ለሚደረግ ማንኛውም የዳሰሳ ጥናት የገንዘብ ድጋፍ መኖር ወይም አለመኖር ላይ ሳይመረኮዝ። ወላጆች እና ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ጥበቃ የተደረገላቸውን ግላዊ የመረጃ መደቦችን ስለሚያካትት የዳሰሳ ጥናት የማካሄድ አላማ ቀደም ብሎ በፅሁፍ ማሳወቂያ ሊደርሳቸው ይገባል።

2. ትምህርት መከታተልን እንደ ቅድመ ሁኔታ በመውሰድ ማንኛውም ድንገተኛ ባልሆነ ምክንያት የሚደረግ የሰውነት አካላዊ ምርመራ ወይም ግላዊ አካልን መፈተሽ፣ በት/ቤቱ ወይም በወኪሉ የሚካሄድ እና አፋጣኝ/በወቅቱ በት/ቤቱ የታቀደ፤ የተማሪን ወይም የሌላ ተማሪን ጤና ወይም ደህንነት ለመጠበቅ አስፈላጊ ያልሆነ (የፍሉ ክትባት የመሳሰሉ ነገሮች)፣ ነገር ግን ማዳመጥ፣

እይታ ወይም የስኮሊዎሲስ (scoliosis) ምርመራ፣ ወይም የተፈቀደ ወይም በስቴት ህግ ስር መሟላት ያለበት ማንኛውንም አካላዊ ምርመራን አያካትትም።

3. በ IV ውስጥ በተጠቀሱት ልዩ ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ከተማሪዎች የተገኘን የግል መረጃ መሰብሰብ፣ መግለጽ ወይም ለገበያ ወይም ለሽያጭ ማቅረብ ወይም ለሌላ ሦስተኛ ወገን መረጃ ማሰራጨትን የሚያካትቱ ተግባራት።

D. አንዳንድ እቃዎችን መፈተሽ። ለዳይሬክተር ወይም ለተወካይ በሚቀርብ የፅሁፍ ጥያቄ መሰረት፣ MCPS ጥቅም ላይ ከማዋሉ በፊት ወላጆች እና ብቁ የሆኑ ተማሪዎች የሚከተሉትን የመመርመር መብት አላቸው:-

1. ጥበቃ የሚደረግለት የመረጃ መደቦችን የሚያካትቱ የዳሰሳ ጥናቶች፣ ማንኛውንም ጥበቃ የሚደረግለት የመረጃ ዳሰሳ ጥናት ጋር የሚገናኝ ጥቅም ላይ የዋሉ የትምህርት መሳሪያዎች ጭምር።

2. ማንኛውም ከላይ ለተጠቀሱት ለማስተዋወቅ ወይም ለሽያጭ ወይም ለሌሎች መረጃን ለማሰራጨት አላማ ከተማሪዎች የግል መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋሉ ዶክመንቶች/ሰነዶች።

3. የስርዓተ ትምህርት አካል ሆነው ጥቅም ላይ የሚውሉ ለተማሪዎች የተሰጡ የትምህርት መሳሪያዎች (በአስተማሪዎች ጥቅም ላይ ከዋሉ ፈተናዎች፣ የሙከራ ቴስቶች እና ምዘናዎች በስተቀር)።

E. ጥሰቶችን ሪፖርት ስለማድረግ ወላጆች እና ብቁ ተማሪዎች በዚህ ደንብ ውስጥ የተቀመጡትን መስፈርቶች ለማክበር በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚከሰቱ ጥሰቶችን በሚመለከት ለዩኤስ የትምህርት ዲፓርትመንት ቅሬታ የማቅረብ መብት አላቸው።

IV. የማይካተቱ ልዩ ሁኔታዎች:-

A. ለማስተዋወቅ አላማ ከተማሪዎች የግል መረጃ መሰብሰብ እና ይፋ ማድረግ ጋር ለሚገናኙ ተግባራት የተቀመጡት መስፈርቶች ተፈፃሚ የማይሆኑት ትምህርታዊ ግብዓቶችን/እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ለተማሪዎች ወይም የትምህርት ተቋማትን አካታች ለሆኑ አላማዎች ማዘጋጀት፣ መመዘን ወይም ማቅረብ ሲሆን ይኼውም የሚከተሉትን ያካትታል:-

1. የኮሌጅ ወይም ሌላ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ምልመላ፣ ወይም ወታደራዊ ምልመላ።

2. የመፅሀፍት ክለቦች፣ መፅሔቶች እና ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው የስነ-ጽሁፍ ምርቶችን የሚያቀርቡ ፕሮግራሞች።

3. በት/ቤቶች ጥቅም ላይ የሚውሉ የስርዓተ ትምህርት እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች።

4. ስለ ተማሪዎች እውቀት፣ የምዘና፣ የምርመራ፣ የክሊንክ፣ የብቃት ወይም የውጤት መረጃ ለማቅረብ እና ከእነዚህ አይነት ፈተናዎች እና ምዘናዎች አጠቃላይ መረጃዎች በቀጣይነት ለመገምገም እና ለህዝብ ይፋ ለማድረግ በት/ቤቶች ጥቅም ላይ የሚውሉ ፈተናዎች እና ምዘናዎች።

5. በት/ቤት ስፖንሰር ለሚደረጉ ወይም ከትምህርት ተዛማጅ ለሆኑ ተግባራት ገንዘብ ለማሰባሰብ በተማሪዎች የሚደረግ የምርቶች/የእቃዎች ወይም አገልግሎቶች ሽያጭ።

6. ለተማሪ የእውቅና መስጫ ፕሮግራሞች።

B. አካላዊ ምርመራዎችን በሚመለከት የተቀመጡት መስፈርቶች የማዳመጥ፣ የእይታ ወይም የስኮሊዎሲስ (scoliosis) መለያ ምርመራን፣ ወይም በስቴት ህግ ስር የተፈቀደ ወይም መሟላት ያለበት፣ እና ለቤተሰብ ማሳወቂያ ሳይሰጥ የተፈቀደን ማንኛውንም አካላዊ ምርመራን ወይም መለያ ምርመራን አያካትቱም።

C. የትምህርት መሳሪያዎችን መፈተሽን በሚመለከት የተቀመጡት መስፈርቶች ትምህርታዊ ፈተናዎችን፣ የሙከራ ቴስቶችን እና ትምህርታዊ ምዘናዎችን የመመርመር መብትን አያካትቱም።

የደንቡ ታሪክ፡ አዲስ ደንብ ሴፕቴምበር 12, 2008።